# በኢትዮጵያ ገለልተኛ የሆነ የመረጃ ጥበቃ ስርዓት እንዲዘረጋ የሚያስፈልጉ መርሖዎች

## የፖሊሲ ጥቆማ

CARD
የመብቶች እና ዲሞክራሲ ዕድገት ማዕከል
CENTER FOR ADVANCEMENT OF RIGHTS AND DEMOCRACY

adapt

አዘጋጅ ዮሐንስ ኢያሌው

## መግቢያ

ኢትዮጵያ ***በመረጃ ጥበቃ ረቂቅ አዋጅ*** መሠረት ገለልተኛ የሆነ የመረጃ ጥበቃ ኮሚሽን ለማቋቋም በዝግጅት ላይ ትገኛለች። አዋጁ ከፀደቀ በኋላ በኮሚሽኑ አማካይነት የዳታ አጠቃቀምን የሚቆጣጠር እና የኢትዮጵያውያንን የግል መብት የሚጠብቅ ይሆናል። በተለይም ረቂቁ አዋጁ የግለሰቦችን መሰረታዊ መብቶች ለማስጠበቅ የተለመዱት የሰብዓዊ መብት ሕጎች ከሚደነግጉት ሰፋ ባለ መልኩ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸውን የግለሰብ ዳታ አይነቶች እንዲቆጣጠሩ ፈቃድ የሚሰጥ ነው።[1] በእርግጥ የግለሰብ መብት በሕገ መንግሥቱም የተረጋገጠ ነው።[2] በተጨማሪም ረቂቅ አዋጁ፤ የባለድርሻ አካላትን መብት እና ግዴታ ያስቀምጣል፣ ተመሳሳይ ጉዳዮችን የማስተዳደር ሥልጣን አለው እንዲሁም ጠንካራ የግል ዳታ ጥበቃ ባህል እንዲኖር የሚያረጋግጥ ሥርዓት ይዘረጋል።

ነገር ግን ግለሰቦች እና ቡድኖች የግል መረጃዎቻቸውን የመቆጣጠር መብታቸው የተሻለ እንዲሆን ረቂቅ አዋጁ ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች እንዳሉት ሆነው፤ ጠንካራ እና ገለልተኛ የመረጃ ጥበቃ ኮሚሽን እንዲቋቋም ማመቻቸት አለበት።

ይህ የፖሊሲ ጥቆማ ለሚመለከታቸው የሕግ አርቃቂዎች እና አጽዳቂ አካላት፤ ነፃና ገለልተኛ የመረጃ ጥበቃ ኮሚሽን ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑን ለማሳወቅ ይፈልጋል። ኮሚሽኑ ብቁ እና ተቋማዊ ጥንካሬ ያለው ሊሆን ይገባል። ይህን እውን ለማድረግ ኮሚሽኑ የበጀት እና የሠራተኛ አቅም እንዲሁም የሚታወቅ ሥልጣን እና የመዳኘት ኃላፊነት እንዲኖረው በአዋጁ በግልፅ መደንገግ አለበት። በተጨማሪም የጥቅም ግጭት ካላቸው የግል ተቋማት ጣልቃ ገብነት እንደማይኖር ሊረጋገጥ ይገባል።

## የገለልተኛ ኮሚሽን አስፈላጊነት

ገለልተኛ የመረጃ ጥበቃ ኮሚሽኖች **"የግል ዳታ ጥበቃ የበላይ ጠባቂዎች"**[3] ተደርገው ይወሰዳሉ። ስለሆነም ***ገለልተኛ የመረጃ ጥበቃ ኮሚሽን*** ማቋቋም በዲሞክራሲያዊ ማበረሰብ ውስጥ የመረጃ ጥበቃ እና የግል መብት መሰረት ነው ማለት ይቻላል። የግል መረጃ ጥበቃ ረቂቅ አዋጁ አንቀጽ **4(1) ገለልተኛ የሆነ የመረጃ ጥበቃ ኮሚሽን** በኢትዮጵያ እንደሚቋቋም ይደነግጋል። ይሁን እንጂ ኮሚሽኑ በአዋጁ መሠረት ተግባራቱን ለመወጣትና ሥልጣኑን ለመጠቀም በ **"ሙሉ"** ነፃነት እንደሚሠራና እንደማይሠራ ረቂቅ አዋጁ በግልጽ ያስቀመጠው ነገር የለም። ኮሚሽኑ መሠረታዊ የግል መብቶችን እና የግል መረጃ ጥበቃን የመቆጣጠር እና የመምራት ኃላፊነት ስላለበት ለመረጃ ጥበቃ ኮሚሽኑ ሙሉ ነፃነት መስጠት በጣም አስፈላጊ ነው። እንዲሁም የግል መብቶችን እና የመሳሰሉ ሕገ መንግሥታዊ መብቶችን የመጠበቅ ኃላፊነት ለኮሚሽኑ ተሰጥቶታል።

ስለዚህ፣ ኮሚሽኑ ***"ሙሉ"*** ነፃነት ሊኖረው ገባል ስንል ***"ሙሉ"*** የሚለው ቅጥያ የመረጃ ጥበቃ ኮሚሽኖች የሚያስተላፉት ወይም የሚሰጡት ማናቸውም ውሳኔዎች ከማንኛውም የውጭ አካል ከሚደርስ ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ተጽዕኖ ነፃ ሆነው በፍፁም ነፃነት እየሠሩ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው። በመጨረሻም የኮሚሽኑ ገለልተኛ መሆን በግል መረጃዎች ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር ከግል መረጃ ጥበቃ ደንቦች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን በማድረግ ውጤታማ እና አስተማማኝነቱን የሚያረጋግጥ ይሆናል።[4] በዋነኝነት ደግሞ ***የመረጃ ጥበቃ ኮሚሽኑ*** ከሶስት አካላት ተጽዕኖ ነፃ መሆን አለበት። እነዚህም፡-

የጥቅም ግጭት ያላቸው የግል ድርጅቶች፣ መንግሥት እና ዓለም አቀፍ ተቋማት ናቸው። [5]




## ***ሥልጣኑ ለማን ይሰጥ፡***
## ***ለፌዴራል? ለክልሎች? ወይንስ የጋራ ይሁን?***

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የፌደራል ሥርዓትን በሚከተሉ አገሮች የኮሚሽኑ የሥልጣን ባለቤትነት ጉዳይ በተመለከተ ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። በፌደራል ሥርዓት የምትተዳደረው ቤልጂየም የመረጃ ጥበቃ ሕግ የማስፈጸምን ሥልጣን ለፌደራል መንግሥት ሰጥታለች። እ.ኤ.አ. በ**2021** የፀደቀ የህንድ የዳታ ጥበቃ አዋጅ ***የዳታ ጥበቃ ባለሥልጣን*** የሚባል ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በማዕከላዊ ወይም ፌዴራል መንግሥት አካል ሆኖ እንዲቋቋም ያዛል። በጀርመን ደግሞ አገሪቱ በጥምር የምትመራ በመሆኗ የመረጃ ነፃነትን እና የግል ዳታ ጥበቃ ጉዳዮችን በተመለከተ ***የፌደራል ዳታ ጥበቃ ሕግ***ን በፌደራል የሚገኘው የዳታ ጥበቃ ኮሚሽን በበላይነት የሚቆጣጠር ሲሆን፣ በ**16** ክልሎች ግን ራሳቸውን የቻሉ የዳታ ጥበቃ ባለሥልጣናት ተቋቁመዋል። የኢትዮጵያን የመረጃ ጥበቃ ረቂቅ አዋጅ አንቀጽ **7** ስንመለከት ደግሞ ኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤቱን አዲስ አበባ አድርጎ በኢትዮጵያ ውስጥ በማንኛውም ቦታ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ሊኖረው እንደሚችል ይደነግጋል። ረቂቅ አዋጁ የፌዴራል መንግሥት በሀገሪቱ የመረጃ ጥበቃ ጉዳይ ላይ ልዩ ሥልጣን እንዳለው ያስቀምጣል።

ይሁን እንጂ ***በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር (MiNT)*** የተዘጋጀው የመረጃ ጥበቃ ረቂቅ አዋጅ ***ከፍትሕ ሚኒስቴር*** ተቃውሞ ገጥሞታል። ፍትሕ ሚኒስቴር የመረጃ ጥበቃ ጉዳይ የወንጀል ሕግ ውስጥ የሚካተት በመሆኑ የክልል መንግሥታትን የሚመለከት እንጂ የፌደራል መንግሥት ጉዳይ መሆን የለበትም በማለት መከራከሪያ ያቀርባል። በተለይም ደግሞ የግል መረጃ ጥበቃ ጉዳይ የወንጀል መከላከል አካል እንደመሆኑ መጠን ረቂቅ አዋጁ ሕገ መንግሥቱ ለክልል መንግሥታት የሰጠውን ሥልጣን የሚሸረሽር በመሆኑ ሥልጣኑ ለክልል መንግሥታት ሊሰጥ ይገባል ሲል የፍትሕ ሚኒስቴር ይሟገታል። [6]

***የፍትሕ ሚኒስቴር*** መከራከሪያ ነጥብ ትክክል ቢሆንም፤ የግል ዳታ ጥበቃን እንደ የወንጀል ሕግ ጉዳይ እንደሆነ ማስቀመጥ ከአቅላይነት/ሪዳክሽኒስት ፍልስፍና የመጣ ይመስላል። ***የመረጃ ጥበቃ*** የመረጃ ባለቤቶችን መሠረታዊ መብቶች መጠበቅ እና የግል ዳታ የማቀናበር ሂደትን ለማስተዳደር መስፈርቶችን ማዘጋጀት ማለት ነው። ስለሆነም የመረጃ ጥበቃ ጉዳይ ከወንጀል ጉዳይ ይልቅ በአብዛኛው የሰብዓዊ መብቶች፣ የአስተዳደር ሕግ፣ የፍትሐ ብሔር ሕግ እና ከውል ውጪ የተቀመጡ ሕጎችን የሚመለከቱ ገጽታዎች ይኖሩታል ማለት ነው። በሌላ በኩል የረቂቅ አዋጁ አዘጋጅ የሆነው ***ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር (MiNT)*** የመረጃ ጥበቃ ጉዳይ የፍትሐ ብሔር ሕግ ጉዳይ እንደሆነ ይገልጻል። በእርግጥም የእነሱ መከራከሪያ ነጥብ ሥልጣን ለክልል መንግሥታት ሳይሰጥ የመረጃ ጥበቃ አዋጁ በፌደራል መንግሥት አማካይነት ወጥ በሆነ መልኩ መተግበር አለበት የሚል ነው። ይህም የሕገ መንግሥቱ አንቀፅ **55(6)**ን መሠረት ያደረገ ሲሆን፣ የፌደሬሽን ምክር ቤት አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመመሥረትና ለማስቀጠል አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን የፍትሐ ብሔር ሕጎች የፌዴራል መንግሥት እንዲቆጣጠር የሚደነግግ ነው። የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር **(MINT)** መከራከሪያ ሃሳብ አሳማኝ ቢመስልም የመረጃ ጥበቃ ሕግን ሙሉ በሙሉ የፍትሐ ብሔር ሕግ አካል ብቻ አድርጎ ማየቱ እንደ መሠረታዊ መብቶች ጥበቃ ያሉ ሌሎች የመረጃ ጥበቃ እሴቶች እንዲደበቁ ያደርጋል።

ከሁሉም በላይ መሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶችን እና ነጻነቶችን የሚቆጣጠረው ***የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን*** ሥልጣኑ በግልፅ ለፌዴራል መንግሥት እስከተሰጠ ድረስ፤ በተመሳሳይ መልኩ መሠረታዊ የሆኑ ሰብዓዊ መብቶችን እና ነጻነቶችን ይቆጣጠራል ተብሎ የሚጠበቀው የመረጃ ጥበቃ ኮሚሽን ሥልጣን ለፌደራል መንግሥት መሰጠት አለበት። የሕገ መንግሥቱን አንቀፅ **51(3)** እና አንቀፅ **55(5)**ን ስንመለከት የፌደራል መንግሥት የመረጃ ጥበቃን ጨምሮ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ሕጎችን እና ሀገር ዓቀፍ መመሪያዎችን የማውጣት ሰፊ ሥልጣን እንዳለው እንመለከታለን። ስለሆነም የሕጉ አተገባበር በመላው ሀገሪቱ ወጥነት እንዲኖረው የግል መረጃ ጥበቃን የሚመለከተው ሥልጣን ከክልል መንግሥታት ይልቅ የፌደራል መንግሥት ሥልጣን መሆን አለበት የሚል አቋም አለን።

## ኮሚሽኑንን በመቅር፣
## በሀብት እና በሥልጣን ብቁ ማድረግ

የማንኛውም የመረጃ ጥበቃ ኮሚሽን ገለልተኝነት ቢያንስ በስት መስፈርቶች ሊለካ ይችላል። እነሱም የአደረጃጀት መዋቅር፣ ሀብት እና ሥልጣን ናቸው። በአደረጃጀትና መዋቅር ረገድ በረቂቅ አዋጁ በአንቀጽ **6** መሠረት ኮሚሽኑ ኮሚሽነር፣ ምክትል ኮሚሽነሮች እና ሌሎች አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል። ሆኖም ግን በረቂቅ አዋጁ አስፈላጊ ሠራተኞች የተባሉትን በተመለከተ በግልፅ አያስቀምጥም። ኮሚሽኑ እንዴት መደራጀት እንደሚገባው በአዋጁ በዝርዝር እንዲካተት ስንል ምክረ ሐሳባችንን በአፅንኦት እናቀርባለን። ከሌሎች አገሮች ጋር ስናነፃፅረው የመረጃ ጥበቃ ኮሚሽን በቂ የሥራ ክፍሎች ሊኖሩት እንደሚገባ እንረዳለን። ከኮሚሽነር እና ምክትል ኮሚሽነሮች በተጨማሪ፤ የፋይናንስ ክፍል፣ የሕግ እና የቁጥጥር ክፍል፤ የምርምር፣ ልማት እና ፈጠራ፤ የትብብር እና ኮሙኒኬሽን እንዲሁም ሌሎች ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ያስፈልጉታል።

የኮሚሽኑን ገለልተኛነት የሚያረጋግጠው ዋነው ጉዳይ ከፖለቲካ ፓርቲ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ገለልተኛ የሆኑ ኮሚሽነር(ሮች)ን መሾም ነው። ሆኖም የመረጃ ጥበቃ ኮሚሽነር እና የሦስቱ ምክትል ኮሚሽነሮች አመራረጥ እና ሹመት እንዴት እንደሚካሄድ በረቂቅ አዋጁ ላይ ዝርዝር መመሪያ አልሰጠም። በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ **10(1)** ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አምስት አባላት ያሉት ገለልተኛ ኮሚቴ እንደሚያቋቁም እና ይህ ኮሚቴም ለኮሚሽነርና ለምክትል ኮሚሽነርነት የዕጩዎች ምልመላ እንደሚያካሂድ ይገልጻል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ የዕጩዎችን ዝርዝር ከተቀበለ በኋላ የተመረጡ

ዕጩዎቹ በመለየት በምክር ቤቱ እንዲሾሙ ያቀርባቸዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኮሚሽነሮችን የመምረጥ ሥልጣን ካለው የኮሚሽኑ ሥራ በአስፈፃሚው አካል ተጽዕኖ ሊደርስበት እንደሚችል አመላካች ነው።

ገለልተኛ የሆኑ የመረጃ ኮሚሽነሮች ሥራ ከማንኛውም ከፍተኛ አስፈፃሚ አካል ጣልቃ ገብነት ነፃ መሆን ስለሚኖርበት፤ የኮሚሽኑ "ሙሉ ነፃነት"ን የማረጋገጥ ሥራ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ነው። በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ **10(1)** የተመለከተው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣን እንደገና መከለስ ያለበት ሲሆን፣ ሥልጣኑ ለምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ ተሰጥቶ በምክር ቤቱ ልዩ ኮሚቴ መመራት ይኖርበታል። እንደ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ያሉ ነባር ኮሚሽኖችን ኮሚሽነር በሚሾምበት ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዋና ኮሚሽነር መርጦ ለምክር ቤቱ አቅርቦ እንደሚያስጸድቅ የሚታወቅ ነው።

**ኮሚሽነሮች ከሌላ ዘርፍ ተደራቢ ኃላፊነት መውሰድ የለባቸውም።** የኮሚሽኑን ሙሉ ገለልተኛነት ለማረጋገጥ ኮሚሽነሮች የጥቅም ግጭት ጉዳይ እንዳይኖር የገለልተኛ የመረጃ ጥበቃን ሚና እና ተግባራቸውን የሚቆጣጠር ድንጋጌ በረቂቅ አዋጁ መካተት አለበት። ኮሚሽነሮች በሌሎች ኮሚቴ ወይም የመንግሥት ፕሮጀክቶች ውስጥ እና ተያያዥ ጊዜያዊ ሥራዎች ውስጥ ሚና ሊጫወቱ አይገባም። እንዲሁም በግልም ሆነ በሌሎች ዘርፎች ሥር ዳታ ከሚቆጣጠሩ፣ ከሚያቀናብሩ ወይም የኮሚሽኑን ነፃነት እና ገለልተኝነት የሚያዳክም ሥራ ከሚሰሩ አካላት ጋር መተባበር ወይም መሥራት የለባቸውም።

ረቂቅ አዋጁ በአንቀጽ **10(6)** ላይ የኮሚሽነሮችን የትምህርት መመዘኛ መስፈርት በዝርዝር ያስቀምጣል። በዚህም መሰረት ማንኛውም ሰው በሕግ፣ በዳታ ሳይንስ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ወይም በሌላ አግባብነት ያለው የትምህርት ዘርፍ የሰለጠነ ወይም በልምድ ሰፊ እውቀት ያለው ሰው ሊሾም እንደሚገባ ተቀምጧል። ይሁን እንጂ በረቂቅ አዋጁ ከትምህርት ዝግጅት እና ብቃት ጋር በተያያዘ የኮሚሽነሮችን ስብጥር ምን መሆን እንዳለበት አልተቀመጠም። የመረጃ ጥበቃን መቆጣጠር የሕግ ጉዳዮችን የሚያካትት በመሆኑ ከሦስቱ ኮሚሽነሮች አንዱ ጠበቃ ወይም የሕግ ፕሮፌሰር መሆን እንዳለበት የሚገልጽ ድንጋጌ ቢኖር ጥሩ ነው።

የደቡብ አፍሪካ *የግል መረጃ ጥበቃ አዋጅ* አንቀፅ **41** ላይ ከምክትል ተቆጣጣሪዎች መካከል አንደኛቸው የመብት ተሟጋች ወይም የጠበቃነት ወይም የዩኒቨርሲቲ መምህርነት ልምድ በመያዝ መሾም እንዳለበት ያረጋግጣል ።

**ኮሚሽኑ የተሟላ የፋይናንስ ነፃነት እና በጀት ሊኖረው ይገባል።** መንግስት ለኮሚሽኑ በቂ በጀት መመደብ አለበት።

ይህም ከግል ተቋማት ተጽዕኖ ውጭ ሆኖ ተልዕኮውን እና ተግባራቱን እንዲያከናውን ያስችለዋል። ሆኖም ግን ረቂቅ አዋጁ በአንቀፅ **8** ላይ "አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ከሀገር ውስጥ፣ ከውጭ እና ከዓለም አቀፍ ተቋማት የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት ይቻላል" የሚል ሀረግ ተጠቅሟል። ይህም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኮሚሽኑ በገንዘብ ራሱን እንዳይችል ጣልቃ በመግባ በስተመጨረሻም የኮሚሽኑን ገለልተኝነት ላይ ተጽዕኖ ሊያመጣ ይችላል። በመሆኑም ይህ ድንጋጌ "አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የኮሚሽኑን ነፃነት እስካልነካ ድረስ ወይም ዕርዳታው ዳታ ተቆጣጣሪ ከሆነ ድርጅት እስካልመጣ ድረስ፤ ከአገር ውስጥ፣ ከውጪ ወይም ከዓለም አቀፍ ተቋማት የገንዘብ ድጋፍ ሊደረግለት ይችላል" በሚል እንዲስተካከል እንመክራለን። የኮሚሽኑ ነፃነት ሲባል ግን የፋይናንስ ወጪን ወይም ሥልጣኑን በሚመለከት ቁጥጥር ወይም ክትትል ሊደረግበት አይችልም ወይም ኮሚሽኑ ለሠራተኞቹ የአቅም ግንባታ ሥራዎች የዓለም አቀፍ ድርጅቶችን ድጋፍ ሊጠይቅ አይችልም ማለት አይደለም።

**ረቂቅ አዋጁ በአንቀፅ 5 ላይ ለኮሚሽኑ ሰፋ ያለ ሥልጣን ተሰጥቶታል።** ከተዘረዘሩት ስሥልጣኖች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል። አዋጁ መፈጸሙን ማረጋገጥ፣ ማዕቀብ/ቅጣት መጣል፣ ስለ ግል መረጃ ጥበቃ ኅብረተሰቡን ማስተማር/ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ የግል ዳታን እና ልዩ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸውን ዳታዎችን ቅንብር የመቆጣጠር፣ ምርመራ ማካሄድ፣ ዳታ ተቆጣጣሪ ወይም አቀናባሪ ላይ አስገዳጅ ትዕዛዝ ማውጣት እና ሌሎች የአዋጁን ዓላማዎች ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ

ተግባራትን ማከናወን ለኮሚሽኑ ከተሰጡ ኃላፊነቶች መካከል አንዱ ነው። ከኮሚሽኑ ሥልጣን እና ኃላፊነት ጋር በተያያዘ ረቂቅ አዋጁ ጥሩ ይመስላል። ነገር ግን አንቀጽ 5(18) ኮሚሽኑ የሥልጣን ባለቤት እንዲሆን በሚያስችለው መለኩ እንደገና መታየት እንዳለበት ለማመላከት እንወዳለን።

አጠራጣሪ ሁኔታዎች በሚገጥሙበት ጊዜ በግልጽ ያልተሰጡ ሥልጣኖች ኮሚሽኑ ተልዕኮውንና ዓላማውን እንዲያሳካ ከወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ሊተረጎሙ ይችላሉ። በተጨማሪም ኮሚሽኑ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 63(5) ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በልዩ ሁኔታ የሚሰጠውን ውሳኔ በተመለከተ የመቆጣጠር ሥልጣን ሊኖረው ይገባል። አንቀጽ 63(3) እንዲህ ይላል፡- "የዚህ አዋጅ ማናቸውም ድንጋጌዎች በግል ዳታ ላይ ተፈጻሚ እንዳይሆኑ ገደብ የሚጣልባቸው፣ ድንጋጌዎቹ በግል ዳታ ላይ ተፈጻሚ እንደማይሆኑ በጠቅላይ ሚኒስቴሩ ውሳኔ ብሔራዊ ደኅንነትን፣ የአገር መከላከያን እና የሕዝብ ሠላምን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ከሆነ ነው።"

በሌሎች አካባቢዎች፣ በሕጉ መሠረት ተፈፃሚ እንዳይሆን ገደብ የሚጣልበት የግል መረጃ በሚወሰንበት ጊዜ የዳኝነት ምርመራም አብሮ ይካሄዳል። በተመሳሳይም የረቂቅ አዋጁ በአንቀፅ 63(3) ላይ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ብቻ የተሰጠው ገደብ የመጣል ሥልጣን፤ ውሳኔ ከማግኘቱ በፊት በኮሚሽኑ እንዲመረመር እና ተገቢነት ባለው የፍትሕ አካል እንዲታይ እንመክራለን።

## ምክረ ሐሳቦች

የኢትዮጵያ መረጃ ጥበቃ ኮሚሽንን ገለልተኛ ለማድረግ እንዲያስችሉ ይረዳ ዘንድ የሚከተሉትን ምክረ ሐሳቦች እናቀርባለን።

- የግል ተቋማት በገንዘብ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያደርጉት ተፅዕኖ ኮሚሽኑ በነፃነት ሥራውን እንዳያከናውን በማድረግ ኮሚሽኑን ሥራ ያደበዝዛሉ። በመሆኑም ኮሚሽኑ ከግሉ ዘርፍ፤ በተለይም ከመረጃ ተቆጣጣሪዎች፣ የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮች፣ የኢንተርኔት አቅራቢዎች፣ የቴሌኮሙኒኬሽን አቅራቢዎች እና ከሌሎች ተመሳሳይ የንግድ ተቋማት የገንዘብ ድጋፍ እንዳያገኝ እንመክራለን።
- የኮሚሽኑን ሙሉ ነፃነትን ማረጋገጥ ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚጠይቅ በመሆኑ፤ በአንቀጽ 10(1) ላይ የተመለከተው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣን እንደገና እንዲታይና ሥልጣኑ ለምክር ቤቱ አፈ-ጉባዔ ተሰጥቶ በመጨረሻ በምክር ቤቱ ልዩ ኮሚቴ እንዲገመገም ቢደረግ።
- ሕገ መንግሥቱ የዳታ ጥበቃን የሥልጣን ባለቤት በሚመለከት ግልጽ መመሪያ ባይኖረውም፣ የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 51(3) እና 55(5)ን ትርጓሜ በመውሰድ የፌደራል መንግሥት የመረጃ ጥበቃ ሕግ የማውጣትና ተቆጣጣሪ ኮሚሽኑን የማቋቋም ሥልጣን ሊኖረው ይገባል እንላለን።
- በመጨረሻም፤ ኮሚሽኑ "ሙሉ" ነፃነት እንዲኖረው በአዋጁ ላይ በጽሑፍ የተቀመጠ ማረጋገጫ ሊኖረው ይገባል። እነዚህን ምክሮች ከግምት ውስጥ በማስገባት ረቂቅ አዋጁ በአስቸኳይ ሊፀድቅ እንደሚገባ እናምናለን።

## ዋቢ ሰነዶች

[1] የኢትዮጵያ የግል መረጃ ጥበቃ (ረቂቅ አዋጅ 2013) መግቢያ አንቀጽ 3. የአውሮፓ ህብረት የዳታ ጥበቃ ሕግ መሠረቶች በኦርላ ሊንስኪ (በኦክስፎርድ ዩንቨርስቲ የታተመ፤ 2007) 11

[2] የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት፤ ነሐሴ 1987፣ ፌደራል ነጋት ጋዜጣ ቁጥር 1፣ አዲስ አበባ፣ አንቀፅ 26።

[3] አውሮፓ ሕብረት በጀርመን መንግስት ላይ ያቀረበው ክስ፤ CJEU መዝገብ ቁጥር C-518/07 EU:C:2010:125 ፤ አንቀፅ 23

[4] አውሮፓ ሕብረት በሐንጋሪ መንግስት ላይ ያቀረበው ክስ፤ መዝገብ ቁጥር C-288/12, EU:C:2014:237 ፤ አንቀፅ 48

[5] የአውሮፓ ህብረት የበይነመረብ ሙብት ጠባቂ፤ በሂኪ ሂጅማስ (springer.com ላይ በ2008 የታተመ) ገጽ 360

[6] **Selamawit Mengesha, 'Quarrel over regional states' autonomy delays data protection bill,' (The Reporter, August 6, 2022) < https://www.thereporterethiopia.com/25605/#> accessed August 22, 2022.**